# የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችን በመንግስትና በግል አጋርነት ለማስተዳደር የወጣ መመሪያ ቁጥር 838/2014

የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ሀብት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም እንዲሁም የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ስርዓተ አያያዝን የግል ዘርፉና የህብረተሰቡ ተሳትፎን በማጎልበት እየደረሰባቸው ካለው አደጋ እንዲያገግሙ በማድረግ ሃብቱን በተገቢ ሁኔታ መጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የጥበቃ ቦታዎች ሥርዓተ-አያያዝ ከፍተኛ መዋእለ ንዋይ የሚጠይቅና ይህም በመንግስት ብቻ መሸፈን የማይቻል በመሆኑና የግል ዘርፉንና ህብረተሰቡን ማሳተፍ በማስፈለጉ፤

የዱር እንስሳት ሀብቱን ለመጠበቅና ለማልማት የሚያስችል አጋርነትን በማስፋፋት እና አካባቢያዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች ይበልጥ በማሳደግ አገሪቱ በዘርፉ ተወዳዳሪ እና ተመራጭ የምትሆንበትን መንገድ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

ኮሚሽኑ በአዋጅ ቁጥር 541/1999 አንቀጽ 6 እና 13 ንዑስ አንቀጽ 1 እንዲሁም አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 2፣ በአዋጅ 575/2000 አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 12 እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 33/25/ሐ መሰረት ይህን በመንግስትና በግል አጋርነት የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችን ለማስተዳደር የሚያስችለውን ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## የክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ፤

ይህ መመሪያ "የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችን በመንግስትና በግል አጋርነት ለማስተዳደር" የወጣ መመሪያ ቁጥር 838/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ፤

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "**አዋጅ**" ማለት የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 ነው፡፡
2. "ደንብ " ማለት የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ደንብ ቁጥር 163/2001 ነው፡፡
3. በአዋጁና በደንቡ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
4. "**የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታ**" ማለት ለዱር እንስሳት ጥበቃ በሕግ የተከለለ ሥፍራ ሲሆን ብሔራዊ ፓርኮችን፣ የዱር እንስሳት መጠለያዎችን፣ የዱር እንስሳት ጥብቅ ክልሎችን፤ የዱር እንስሳት የቁጥጥር አደን ቀበሌዎችን፣ የሕብረተሰብ አቀፍ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችን እና ህይወታዊ ጥብቅ ክልሎችን ያጠቃልላል፤
5. "**የመንግስትና የግል አጋርነት የጋራ አስተዳደር**" ማለት ማንኛውም የግል ባለሃብት ወይም ድርጅት ከመንግስት ጋር በሚያደርገው ስምምነት መሠረት የአንድን ወይም ከዚያ በላይ የጥበቃ ቦታዎቹን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለማስተዳደር የሚመሠረት አጋርነት ነው፡፡
6. "**የመንግስትና የግል አጋርነት ስምምነት** " ማለት የመንግስትና የግል አጋርነትን የውል ቃሎችና ሁኔታዎችን በመወሰን በተዋዋይ ባለስልጣን መስሪያቤቱ እና በግል ባለሃብቱ ወይም ድርጅቱ መካከል የሚደረግ ውል ነው፡፡
7. "**አጋር**" ማለት ማንኛውም በህግ የሰውነት ስልጣን የተሰጠው የግል ድርጅት፣ ባለሃብት፣ ወይም ለትርፍ ያልተቋቋመ እና መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም ነው፡፡
8. "**የግል ባለሃብት**" ማለት ከተዋዋይ መንግስታዊ ተቋም ጋር የመንግስትና የግል አጋርነት ስምምነት የሚያደርግ ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል ነው፡፡
9. "**ኮንሴሽን**" ማለት የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችን ለማልማት፣ ለመጠበቅ እና ጥቅም ላይ ለማዋል ለተወሰነ ጊዜ ህጋዊ ሰውነት ላለው አካል በውል ማስተላለፍ ማለት ነው፡፡

10.“የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ” ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት የሚቋቋም በሙሉ ውክል ለአጋሩ የሚተላለፍ አስተዳደርን በበላይነት የሚመራ ኮሚቴ ማለት ነው፡፡

11."**ኮሚሽን**" ወይም "**ኮሚሽነር**" ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው የአከባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ወይም ኮሚሽነር ነው፡፡

12. **“ባለስልጣን”** ማለት የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ነው፡፡

13.**”ባለድርሻ”** ማለት ከባለሥልጣኑ ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሥራ ቅርበትና ግንኙነት ያላቸውና በባለሥልጣኑ ስትራቴጂያዊ እቅዶችና ተግባሮች ላይ ጉልህ ድርሻ ያላቸው አካላት ማለት ነው፡፡

14.**“ሰው”** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

15.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተደነገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## 3. ተፈጻሚነት ወሰን፤

ይህ መመሪያ በአዋጅ ቁጥር 541/1999 እና የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 መሠረት በፌዴራል ስር በሚተዳደሩ የጥበቃ ቦተዎች እና የሦስትዮሽና ከዚያ በላይ ስምምነት የሚገባባቸው ሌሎች የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 4. ዓላማ፤

መመሪያው ከዚህ የሚከተሉት ዋና ዋና ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

1) አዳዲስ ሀሳቦችንና ዘዴዎችን በመጠቀም በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የመንግስት፣ የግሉ ዘርፉ እና የህብረተሰቡ አጋርነትን ማሳደግ፤
2) የመንግስትና የግል ሴክተሩን የሰለጠነ የሰው ኃይል፣ የገንዘብና የቴክኖሎጂ አቅም በማቀናጀት በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ላይ ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት፤

3) አሳታፊ እና ውጤታማ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር በመተግበር የተፈጥሮ ሀብቱ ስነምህዳራዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ማድረግ፣

4) በጥበቃ ቦታዎች የአደጋ መከላከልና ዝግጁነትን በማጎልበት ተጋላጭነትና ስጋትን መቀነስ፡፡

## ክፍል ሁለት

## የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች የመንግስትና የግል አጋርነት አስተዳደር ዓይነት፣ይዘት እና መዋቅር .=

### 5. የአስተዳደር ዓይነቶችና ይዘት

1. ባለስልጣኑ ለአጋሩ በኮንሴሽን ሙሉ ውክልና በመስጠት የሚመሰረት አስተዳደር አይነት ነው፤
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰውን የአስተዳደር አይነት የሚከተለው ይዘት ይኖረዋል፡፡

ሀ) መንግስት ለአንድ አጋር በኮንሴሽን የሚሰጠው ሙሉ ውክልና ላይ የሚመሠረት አስተዳደር፤

ለ) መንግስት ከአንድ በላይ ለሆኑ አጋሮች በኮንሴሽን ሙሉ ውክልና በመስጠት የሚመሠረት አስተዳደር፤

3. ባለስልጣኑ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ አጋሮች ጋር በጋራ ለመስራት የሚመሠረት የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3) የተጠቀሰውን የአስተዳደር አይነት የሚከተለው ይዘት ይኖረዋል፡፡

ሀ) ባለሥልጣኑ ከአንድ አጋር ጋር በእኩል ውክልና የሚመሠረት አስተዳደር፤

ለ) ባለሥልጣኑ ከአንድ አጋር ጋር የሚመሰርተውና የአመራር ሥራ ድርሻው ወደ አንዱ ተወዋዋይ ያመዘነ አስተዳደር፤

ሐ) በመንግስትና ከአንድ በላይ አጋሮች ጋር በእኩል ውክልናና በቅንጅት የሚመሠረት አስተዳደር ናቸው፤

መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ (3) (ለ) እንደተመለከተው የአስተዳደሩ ሚና

ለአንዱ ተዋዋይ ያመዘነ አስተዳደር ላይ ተዋዋዮቹ ከጥበቃ ቦታዎቹመሠረታዊ የሥራ አመራር ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የሚኖራቸው ዝርዝር ድርሻ በሁለቱም ወገኖች በሚፈረመው ስምምነት ላይ የሚገለጽ ይሆናል፡፡

5. በባለስልጣኑ ህጋዊ ሰውነት ካላቸው እና በጥበቃ ቦታዎች ዙሪያ ከሚገኙ የህብረተሰብ አቀፍ አደረጃጀቶች ጋር የሚመሰረት የጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (5) የተጠቀሰውን የአስተዳደር አይነት የሚከተለው ይዘት ይኖረዋል፤

ሀ) በመንግስት ለአካባቢ ማህበረሰብ ሙሉ ውክልና የሚሰጡ የጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር ነው፤

ለ) በመንግስትና በአካባቢ ማህበረሰብ በጋር የሚካሄዱ የኢኮቱሪዝም እና የአከባቢ ተኮር የልማት ስራዎች አስተዳደር ነው፤

## 6. የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር ወዋቅር

1. አንድ ወይም ከአንድ በላይ ለሆኑ አጋሮች ሙሉ ውክልና በመስጠት የሚመሠረትን የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር ስምምነት አፈጻጸም የሚከታተል አጋር ወይም አጋሮቹን ጨምሮ ከልዩ ልዩ ባለድርሻ ተቋማት የተውጣጣ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚኖረው ሆኖ፡-

ሀ) የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሰብሳቢውን ጨምሮ በባለስልጣኑና በአጋር አካሉ በሚደረስ ስምምነት መሰረት በባለስልጣኑ የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል፡፡

ለ) የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው አባላት ከዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ጋር ተያያዥነት ካላቸው መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ ሲቪክ ማህበራት እንዲሁም ከመንግስት አስፈጻሚ ተቋማት የተውጣጡ ሆኖ ቁጥራቸውም እንዳስፈላጊነቱ ይወሰናል፡፡

ሐ) የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በሙሉ ውክልና ለአንድ ወይም ከአንድ በላይ ለሆኑ አጋር አካላቶች የጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር በሙሉ

ውክልና የተሰጠውን ጥበቃ ቦታ አፈጻጸም የሚገመግምበትና ውሳኔ የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

2. ባለስልጣን መስሪያቤቱ ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ ለሆኑ አጋሮች ሙሉ ውክልና በመስጠት የሚመሠረት የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች የሥራ አመራር ስራ የሚመራው በአጋሩ ወይም በአጋሮቹ የአስተዳደር መዋቅር ይሆናል፡፡
3. ባለስልጣን መስሪያቤቱ ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ አጋሮች ጋር በጋራ ለመስራት የሚመሠርተው የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር የሚመራው በአስተባባሪ ኮሚቴ ሆኖ የኮሚቴው ሰብሳቢ ባለስልጣኑ ይሆናል፡፡
4. ባለስልጣን መስሪያቤቱ ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ አጋሮች ጋር በጋራ ለመስራት የሚመሠረት የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች አስተዳደርየጥበቃ ቦታው ስራ አመራር በጋራ ስምምነት በሚመረጥ አንድ ኃላፊ ወይም በአመዛኙ የአስተዳደር ሚና ያለው አጋር አካልበሚመርጠው ኃላፊ የሚመራ ይሆናል፡፡
5. በጥበቃ ቦታዎች ዙሪያ የሚገኙ ህጋዊ ሰውነት ወይም እውቅና ያላቸው የህብረተሰብ አቀፍ አደረጃጀቶች ከባለስልጣኑ እና ከክልሉ የሚለከታቸው አካላት ጋር በሚገቡት የውል ስምምነት መሠረት የሚከናወን የጋራ አስተዳደር ከባለድርሻ አካላት በተውጣጣ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚመራ ይሆናል፡፡
6. የህብረተሰብ አቀፍ አደረጃጀቶች ከባለስልጣኑ እና ከክልሉ የሚለከታቸው አካላት ጋር በሚገቡት የውል ስምምነት መሠረት የአዋሳኝ ማህበረሰብ አደረጃጀት ተወካዮች፣ የጥበቃ ቦታዎች ቺፍ ዋርደኖች እና አጋሮች በሚገኙበት ንኡስ ኮሚቴዎች ይመራል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1)፣ (3) እና (5) የሥራ አስፈጻሚ እና አስተባባሪ ኮሜቴዎች እንደ አሰተዳደሩ ዓይነትና ሁኔታ የየራሳቸውን የአሰራር ስርዓት ይዘረጋሉ፤

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የአዋጭነት ጥናት፣ የተዋዋዮች ስምምነት ይዘት እና</u>

## <u>የማጽደቅ ሂደት</u>

## 7. <u>የአዋጭነት ጥናት ስለማካሄድ</u>

1. የአዋጭነት ጥናት ሥራው ላይ ልምድ ባለው ሕጋዊ እና ገለልተኛ በሆነ አማካሪ ድርጅት አማካኝነት ይከናወናል፤
2. የአዋጭነት ጥናቱ በዋናነት የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤

ሀ) የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ነባራዊ ሁኔታ ጥናት

ለ) የህብረተሰብ ተሳትፎና ተጠቃሚነት

ሐ) የገቢያ ጥናት፤

መ) የገንዘብ ዋጋ ወይም እሴት ትንተና፤

ሠ) ከሚቀርበው የአጋርነት ጥያቄ ጋር በተያያዘ የቴክኒክ እና የህግ ትንተና፤ረ) የአካባቢ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ፤

ሰ) የመንግስትና የግል አጋርነት ስምምነት ዝግጅት አማራጮች፤

ሸ) ለአጋርነት ስምምነቱ ማስፈፀሚያ የሚቀርበው በጀት እና በአፈፃፀም ወቅት የታቀዱ ገቢዎችን እና ወጪዎችን በተመለከተ የፋይናንስ ትንተና፤

## 8. <u>መርሆዎች እና የተዋዋዮች ስምምነት ሠነድ ይዘት፤</u>

1. የጥበቃ ቦታዎች አስተዳደርአጋርነት መርሆዎች የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

   ሀ. ግልፅነትና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፣

   ለ. እኩልነትን ፣ ፍትሐዊነትን እና አሳታፊነትን ማረጋገጥ፣

   ሐ. ውጤታማ ቅንጅት እና ትብብር ማረጋገጥ መ. ከፖሊሲ እና የአሰራር ስርዓቶች ጋር ማጣጣም፤

   ሠ. የሕግ የበላይነትን የማክበር፣

   ረ. የፈጠራ ሂደቶችን እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማበረታታት እና

   ሸ. የተፈጥሮ ሀብት ሥነ-ምህዳራዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳን ማሳደግ እና ዘለቄታን ማረጋገጥ ናቸው፡፡

2. በተዋዋዮች መካካል የሚደረግ ስምምነት ይዘት እንደ አስተደዳደሩ ዓይነት የሚለያይ ሆኖ የሚከተሉትን ጉዳዮች ማካተት አለበት፤

   ሀ) የተዋዋይ ወገኖች ስም እና አድራሻ

ለ) የመንግስትና የግል አጋርነት ርዕስ፤

ሐ) የመንግስትና የግል አጋርነት ስምምነት ዓላማ;

መ) የመንግስትና የግል አጋርነት ስምምነት ቀን፤

ሠ) የተዋዋይ ወገኖች መብቶች እና ግዴታዎች፤

ረ) ቀ) የመንግስትና የግል አጋርነት ስምምነት የውል ዘመን፤

በ) የግጭት አፈታት ዘዴዎች፤

ተ) የተዋዋይ ወገኖች ስምምነትውል ሊቋረጥ የሚችልበት ሁኔታእና ከውሉ በፊት ወደ ነበሩበት የሚመለሱበት ሂደት፣

ቸ) ሕጉን ሳይፃረር በሁለቱም ወገኖች መካከል የተደረጉ ሌሎች ማናቸውም ጉዳዮች፡፡

## 9. <u>የጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር ጥያቄ ስለማቅረብ እና ስምምነት ስለማጽደቅ</u>

1. የተቋሙ ስትራቴጂ ኮሚቴ ሚቀርበውን አስተዳደር ጥያቄና ስምምነት ይህን መመሪያ እና የአዋጭነት ጥናቱን መሠረት በማድረግ የውሳኔ ሃሳብ ለተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ያቀርባል፣
2. ለባለስልጣኑ የሚቀርቡ የአጋርነት ጥያቄዎች የአዋጭነት ጥናቱ በቀረበ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ምላሽ የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የጥበቃ ቦታዎች የጋራ አስተዳደር ዓይነቶች መስፈርቶችን ያሟላ ስምምነት ሰነድ ሲቀርብ በባለሥልጣኑ ይፀድቃል፡፡

# <u>ክፍል አራት</u>

# <u>የተዋዋይ ወገኖችና አስፈጻሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት</u>

## 10. <u>የተዋዋይ ወገኖች ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. የጋራ ተግባርና ኃላፊነቶች

ሀ) በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱት ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው አጋር አካላቶች እና የማህበረሰብ አደረጃጀቶች የሚያስተዳድሯቸውን የመንግሥት እና የግል አጋርነት ጥበቃ ቦታዎች ልማትና ጥበቃ በሚመለከት ሀሳብ የማመንጨት፣

የማቀድ፣ ወሉን የማስተዳደርና አፈጻጸሙን የመከታተል ኃላፊነት ይኖራቸዋል፤

ለ) በየደረጃው ያሉ የተቋማትና የአካባቢውን ህብረተሰብ የሰለጠነ ሰው ኃይል፣ የፋይናስ፣ የመሰረታዊ የመሰረተ ልማት አውታሮች፣ የግብአትና ቴክኖሎጂ ክፍተቶችን በመለየት የአቅም ግንባታ ድጋፍ ያደርጋሉ፤

ሐ) የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታው ሥርዓት-አያያዝ ዕቅድ ያዘጋጃሉ፤ ይከልሳሉ፤

መ) በሚመለከታቸው አካላት መካከል ቅንጅታዊ አሰራር እና የጋራ የኮሚኒኬሽን እና የመረጃ ልውውጥ ስርዓት በመዘረጋት ይተገብራሉ፤

ሠ) የልማትና ጥበቃ ፕሮግራሞች በማስተዋወቅ ኢንቨስትመንትን ያስፋፋሉ፤

ረ) በዚህ መመሪያ መሰረት በየደረጃው ለሚቋቋሙ አደረጃጀቶች ተወካዮቻቸውን ይመድባሉ፤

ሰ) አመታዊ እና የግማሽ አመት የክዋኔ እና የፋይናንስ አፈፃጸምን በሚመለከት ሪፖርቶችን ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ወይም ለአስተባባሪ ኮሚቴ እና ለሚመለከታቸው መንግስታዊ አካላት ያቀርባሉ፤

## 2. የባለስልጣኑ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) በጥበቃ ቦታዎች  ውል የተገባባቸው የውል ስምምነቶች በዚህ መመሪያ እና ሌሎች ህጎች መሠረት መከናወናቸውን ወይም መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤

ለ) አጋር አካሉ ህጋዊ ሰውነት ያለው መሆኑንና አስፈላጊው ሰነድ መቅረቡን እንዲሁም አጋሩ ለትርፍ የተቋቋመ ሲሆን የኢንቨስትመንትና ንግድ ፈቃድ ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፤

ሐ) አጋሩ የአስተዳር ሥራዎችን በስምምነቱ መሰረት በብቃት ማከናወኑን በማረጋገጥ የአጋርነት የውል ስምምነት ጊዜ ገደቡን ይወስናል፤

መ) በስምምነቱ ለሚቀርበው የልማት ተግባር አዋጭነትና በዘርፉ  አገር አቀፍና አለም አቀፍ ልምድና ስኬት ያለው ስለመሆኑ ወይም

በዘርፉ በቂ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች ተካተውበት የተቋቋመ አጋር መሆኑን ያረጋግጣል፤

ሠ) የመንግሥት እና የግል አጋርነትን የሕግ፣ የቁጥጥር፣ የመዋቅር እና የፖሊሲ ማዕቀፍ የሚመለከቱ የውሳኔ ሀሳቦችን አዘጋጅቶ ያጸድቃል፤ ለሚመለከተው አስፈጻሚ ተቋም አቅርቦ ያስጸድቃል፡፡

ረ) ባለስልጣኑ ከዓለም አቀፍ ድጋፍ ሰጪ ተቋማት አጋሮች ትብብርና ድጋፍ የሚያገኙበትን መንገድ የማመቻቸት፣ የማማከር እና የአቅም ግንባታ ድጋፎችን ያደርጋል፡

ሰ) በጥበቃ ቦታዎች ውስጥና አካባቢው የልማት እንቅስቃሴዎች ለማካሄድ የሚያቀርቧቸው የ የልማት ንድፎች በአካባቢያዊ እና ማህበራዊ ተፅእኖ ግምገማ እና በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች የማኔጅመንት ዕቅድ መሠረት ተግባራዊ ሊደረጉ የሚችሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

ሸ) አጋሩ ውል በገባበት ጥበቃ ቦታ ውስጥና አካባቢው ሥራውን ለማካሄድ የሚስችለውን የደህንነት ሁኔታ እንዲኖር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያመቻቻል፤

ቀ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የጥበቃ ቦታዎች አጋርነት አስተዳደርን በሚመለከት የአዋጭነት ጥናት ያሥጠናል፤

በ) ባለስልጣኑ በውል ስምምነት ሰነዱ መሠረት ግዴታቸውን በማይወጡ አጋሮች ላይ ውሉን እና ሌሎች የሀገሪቱን ህጎች መሠረት በማድረግ እርምጃ ይወስዳል፤

ተ) በዚህ መመሪያ መሠረት የመንግሥት እና የግል አጋርነትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉማንዋሎችንና ማስፈጸሚያ ሰነዶችን በማዘጋጀት ያጸድቃል፤ ይተገብራል፤

### 3. በሦስትዮሽ ስምምነት የክልል ተዋዋይ አካል ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች የመንግስትና የግል አስተዳደር የውል ስምምነትን በተመለከተ ክልልሉን በመወከል ይፈጽማል፤

ለ) ከባለሥልጣኑ ጋር በመሆን በጥበቃ ቦታዎች ውል የተገባባቸው ስምምነቶች በዚህ መመሪያ እና ሌሎች ህጎች መሠረት መከናወናቸውን ወይም መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤

ለ) ከጥበቃ ቦታዎች መንግስትና የግል አስተዳደር የውል ስምምነት ከመፈጸሙ በፊት ባለሥልጣኑን ያማክራል፤

ሐ) ከባለሥልጣኑ ጋር በመሆን የውል ስምምነት ጊዜ ገደቡን ይወስናል፤

መ) ከባለሥልጣኑ ጋር በመሆን የመንግሥት እና የግል አጋርነትን የሕግ፣ የቁጥጥር፣ የመዋቅር እና የፖሊሲ ማዕቀፍ የሚመለከቱ የውሳኔ ሀሳቦችን ያቀርባል፤ ያጸድቃል፤

ሠ) በሚመለከታቸው አካላት መካከል ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት በመዘረጋት ይተገብራል፤

ረ) አጋሩ ውል በገባበት ጥበቃ ቦታ ውስጥና አካባቢው ሥራውን ለማካሄድ የሚስችለውን የደህንነት ሁኔታ እንዲኖር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያመቻቻል፤

4. **የአጋሩ ተግባርና ኃላፊነት**

ሀ) አጋሩ በቅድሚያ ወደ መንግስትና የግል አጋርነት ጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር ለመግባት የሚያስችለውን  ህጋዊ ሰውነት ሰነድ ያቀርባል፤

ለ) አጋሩ ወደ መንግስትና የግል አጋርነት ጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር ለትርፍ  የሚገባ ሲሆን ከሚመለከተው መንግስታዊ ተቋም የኢንቨስትመንትና ንግድ ፈቃድ ያቀርባል፤

ሐ)የጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር እና የልማት ተግባራት አግባብነት ባላቸው የሀገሪቱ ህጎች እና ዘርፉን የሚመለከቱ ህግጋቶችን የማክበርና የመተግበር ኃላፊነት አለበት፣

መ)  የጥበቃ ቦታውን አስተዳደር  የአዋጭነት ጥናት ሕጋዊ በሆነ ገለልተኛ አማካሪ ድርጅት አስጠንቶ ሰነድ ያቀርባል

ሠ) በውል ስምምነቱ መሠረት በጥበቃ ቦታ አስተዳደር ለሚቆይበት ጊዜየሚያስፈልገውን የፋይናስ ምንጭና ዝርዝር የስራ እቅድ ያቀርባል ሲፀድቅ ይተገብራል፤

ረ) ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ የማይንቀሳቀሱና ተንቀሳቃሽ መገልገያ መሣሪያዎችን፣ የተሻሻሉ አሰራሮች፣ አደረጃጀቶች፣ ግብአቶች እና ቴክኖሎጂዎችን ያሟላል፤

ሰ) ለጥበቃ ቦታዎች አካባቢ ማህበረሰብ ማህበራዊና ተቋማዊ ኃላፊነቶችን ለመወጣት የሚያስችሉ ተግባራትን ያከናውናል፤

ሸ) የልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ስራው በአካባቢው ህብረተሰብ ባህላዊ፣ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ እሴቶች ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እንዳይፈጥር ያደርጋል፤‹

ቀ) አመታዊ እና የግማሽ አመት የክዋኔ እና የፋይናንስ አፈፃጸምን በሚመለከት ሪፖርቶችን ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እና እንደሁኔታው ለሚመለከታቸው መንግስታዊ አካላት ያቀርባል፤

5. **የተዋዋይ የህብረተሰብ አደረጃጀት ተግባርና ኃላፊነት**

ሀ) የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች የመንግስትና የግል አስተዳደር የውል ስምምነትን በተመለከተ የህብረተሰብ አደረጃጀቱን በመወከል ይፈጽማል፤

ለ) የህብረተሰብ አደረጃጀቱ በቅድሚያ ወደ መንግስትና የግል አጋርነት ጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር ለመግባት የሚያስችለውን ህጋዊ ሰውነት ሰነድ ያቀርባል፤

ሐ) የህብረተሰብ አደረጃጀቱ ወደ መንግስትና የግል አጋርነት ጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር ለትርፍ የሚገባ ሲሆን ከሚመለከተው መንግስታዊ ተቋም የኢንቨስትመንትና ንግድ ፈቃድ ያቀርባል፤

መ) የጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር እና የልማት ተግባራት አግባብነት ባላቸው የሀገሪቱ ህጎች እና ዘርፉን የሚመለከቱ ህግጋቶችን የማክበርና የመተግበር ኃላፊነት አለበት፤

ሠ) የልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ስራው በአካባቢው ህብረተሰብ ባህላዊ፣ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ እሴቶች ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እንዳይፈጥር ያደርጋል፤

ረ) አመታዊ እና የግማሽ አመት የክዋኔ እና የፋይናንስ አፈፃጸምን በሚመለከት ሪፖርቶችን ለአስተባባሪ ኮሚቴ እና እንደሁኔታው ለሚመለከታቸው መንግስታዊ አካላት ያቀርባል፤

ሰ) በዚህ መመሪያ መሠረት የመንግሥት እና የህብረተሰብ አጋርነትን ተግባራዊ ማድረግ የሚያስፈልጉ የማህበረሰብ ተኮር ልማዳዊ አሰራሮችን በማዘጋጀት ያስጸድቃል፣ ይተገብራል፤

ሸ) የህብረተሰብ አደረጃጀቱ የመንግስትና የግል አጋርነት ጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር ሲመሰርት በጥበቃ ቦታው አዋሳኝ የሚገኝ ህብረተሰብ ተሳትፎና ተጠቃሚነት እንዲኖር

## 11. የአስፈጻሚ ኮሚቴዎች ተግባርና ኃላፊነት

### 1. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

ሀ/ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በባለሥልጣኑ የሚመራ ሆኖ ፣ ከአጋሮች እና ከባለድርሻ አካላት የተውጣጡ አባላት ይኖሩታል፤

ለ/ የመንግስት እና የግል አጋርነት ስምምነት ከሀገሪቷ ልዩ ልዩ ፖሊሲዎችና የህግ ማእቀፎች ጋር የተጣጣሙ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

ሐ/ የወል ስምምነት ሰነዱ በተገቢው ሁኔታ መፈጸሙን ይከታተላል፤ በወል ስምምነት ሠነዱ መሠረት እየተፈጸመ አለመሆኑን ባረጋገጠ ጊዜም ባለስልጣኑ አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ እንዲወስድ ያሣውቃል፡፡

መ/ በመንግስት እና የግል አጋርነት ስምምነት ሰነዱ መሰረት የተገኘውን ሀብት ለታለመለት አላማ መዋሉን ይከታተላል፡፡እንዲሁም ዘላቂ የፋይናንስ ምንጭ ስርአት ተዘርግቶ መተግበሩን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

ሠ/ በጥበቃ ቦታው ላይ የሚከናወኑ የልማት ጥያቄዎች እና የገቢ አሰባሰብን

የተማከለ ጉዳዮች ከአጋሩ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በመሮመር የመፍትሔ ሀሳብን ጨምሮ ለአጽዳቂው የማኅበሰት አካል ያቀርባል፡፡

ረ/ ከአካባቢው ህብረተሰብ፣ ከተለያዩ አጋር አካላቶች፣ እንዲሁም ከጥበቃ ቦታው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ካላቸው ማኅበሰታዊ እና ማኅበሰታዊ ያልሆኑ አካላቶችን በማሳተፍ አጋሩ የወል ስምምነቱን ሚፈጸሙ ይከታተላል፡፡

ሰ/ የዱር እንሰሳት ጥበቃ ቦታውን የስርዓት አያያዝ ሁኔታ እና የፕሮግራሞች የዕቅድ ክንውን አፈጻጸምእና ኦዲት ሪፖርቶችን ይገመግሙ፣

ሸ/ **የአስተዳደሩና የስምምነቱ ዓላማዎች ለማስፈጸም አግባብነት ያላቸውን የፌዴራልና የክልል መንግሥታዊ አካላት፤ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፤ የትምህርት ተቋማትና ለጋሽ ድርጅቶች መካከል ትብብር እንዲኖር አስፈላጊ ጥረት ያደርጋል፤**

ቀ) **ከስምምነት ትርጓሜ ጋር ተያይዞ ሊከሰቱ የሚችሉ አለመግባባቶችን መፍትሄ ይሰጣል፤**

በ) **ስምምነት የተገባበት አስተዳደር ለጥበቃ ቦታው ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ውጤታማነትን፣ አዋጭነትን፣ ፍትሐዊነትን፣ ቅንጅታዊነትን፣ ግልጸኝነትን እና ውጤታማ ዓለም አቀፍ ደረጃና ተወዳዳሪነት እሴቶችን መሠረት አድርጎ መተግበሩን ይከታተላል፤ ይገመግማል፤**

ተ/ **ስምምነቱ የህብረተሰብ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ትኩረት ሰጥቶ መተግበሩን ይከታተላል፤**

ቸ/ **የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ለስምምነቱ ተግባራዊነት አስፈላጊውን ድጋፍ የሚያደርግ መሆኑን ይከታተላል፡፡**

## 2. የአስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) **በጥበቃ ቦታዎችና ፕሮጀክቶች በመንግስትና በግል አጋርነት አስተዳደር የልማትና ጥበቃ ስራዎች አስተባባሪ ኮሚቴ በባለስልጣኑ ሰብሳቢነት የሚመራ ሆኖ ከአጋሩ ወይም ከአጋሮች እና በጥበቃ ቦታው ኣዋሳኝ ካሉት ባለድርሻ አካላት የተወጣጡ አባላት ይኖሩታል፤**

ለ) ከሚቴው የሚቀርቡ ዓመታዊ የሥራ ዕቅዶች እና ዓመታዊ በጀቶችን መርምሮ ያጸድቃል፤

ሐ) የጥበቃ ቦታዎች ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ስራዎች ለማከናወን የሚያስፈልጉ የሰው ኃይል፣ የፋይናንስ፣ ቁሣዊ ግብዓትና የቴክኖሎጂ አቅርቦቶች እንዲሟሉ ያደርጋል፤

መ) የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታውና የፕሮጀክቱ የእቅድ ክንውን አፈጻጸም ወርሃዊ፣ የሩብ ዓመትና ዓመታዊ ሪፖርቶች በተያዘላቸው ጊዜ ውስጥ ደረጃቸውን ጠብቀው መድረሳቸውን ያረጋግጣል፤ ሪፖርቶቹን ይገመግማል፤ ግብረመልስ ይሰጣል፤

ሠ) የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታውና ፕሮጄክቱን በተመለከተ የሚቀርብ የክዋኔና የፋይናንስ ኦዲት ሪፖርቶችን ይገመግማል፤ በሪፖርቶቹ መሠረት ተገቢ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል፤

ረ) የአስተዳደሩና የስምምነቱ ዓላማዎች ለማስፈጸም አግባብነት ካላቸው የፌዴራልና የክልል መንግሥታዊ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ይዘረጋል፤

ሰ) ስምምነት የተገባበት አስተዳደር ለጥበቃ ቦታው ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ውጤታማነትን ያረጋግጣል፤

ሸ) የአጋርነት አስተዳደሩ ያልተጠበቁ ድንገተኛ ችግሮች ሲያጋጥሙ አፋጣኝ የመፍትሄ አቅጣጫ ለአስፈጻሚው አካል አቅርቦ ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

## ክፍል አምስት

## የሀብት አጠቃቀም፣ አመራር እና የሚደረጉ ድጋፎች

### 11. የሀብት አጠቃቀምና ክፍፍል፤

1. ውል የተገባበት የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታ የሀብት አጠቃቀምና ክፍፍል በተዋዋዮች መካከል በሚፈረመው የስምምነት ሰነድ መሰረት የሚወሰን ይሆናል፣
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የጥበቃ ቦታው እና በውስጡ ያሉት የተፈጥሮ ሃብቶች ባለቤትነት የህዝብ እና መንግስት እንደሆነ ይቀጥላል፤

3. ውል የተገባበት የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታ የክዋኔና ፋይናንስ ኦዲትን ሪፖርት በየዓመቱ መቅረብ አለበት፤

## 12. አስተዳደርና ፋይናንስ አመራር፤

1. የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታው አስተዳደር በሙሉ ውክልና ለአጋሩ የሚተላለፍ ከሆነ የአስተዳደርና ፋይናንስ አመራርና አደረጃጀት በአስፈጻሚ ኮሚቴ ሲጸድቅ ተግባራዊ ይሆናል፡፡
2. ባለስልጣን መስሪያቤቱ ከአንድ ወይም ከዛ በላይ ከሆኑ አጋሮች ጋር በጋራ ለመስራት የሚመሠረት የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር ላይ የሰው ሃይል ቅጥር፣ ልማትና አመራር፣ የግዥ፣ ንብረትና ፋይናንስ አመራር ሥራዎች የሚፈጸሙት ለአስተባባሪ ኮሚቴ ቀርቦ በሚጸድቀው ዕቅድ መሰረት ሆኖ የሚከተሉትን ሰነዶች መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡
   ሀ) የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታው የሥርአተ-አያያዝ ዕቅድ፤
   ለ) የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታው የቢዝነሰ ዕቅድ፤
   ሐ) የተዋዋዮች ውል ስምምነት፤
   መ) የሰው ሃይል፣ ፋይናንስና ንብረት ምደባና አስተዳደርን በሚመለከት መንግስት ያወጣቸው ህጎች፡፡
3. ባለስልጣን መስሪያቤቱ ከአንድ ወይም ከዛ በላይ ከሆኑ አጋሮች ጋር በጋራ ለመስራት የሚመሠረት የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችአስተዳደር ላይ የመንግስትና የግል አጋርነት አስተዳደሩ የሠራተኞች አፈፃፀምን መሰረት ያደረገ ተጨማሪ ክፍያዎችን ሊፈጽም ወይም ተጓዳኝ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ሊያቀርብ ይችላል፤
4. ባለስልጣን መስሪያቤቱ ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ አጋሮች ጋር በጋራ ለመስራት የሚመሠረት የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር ላይ የመንግስትና የግል አጋርነት አስተዳደሩ የአካባቢው መስተዳድር አካላት ወይም የመማክርት ምክር ቤት በሚሰጡት ውሳኔ መሠረት ከህገ-ወጥ ድርጊት ቅጣትና ውርስ ጋር የተያያዙ ክፍያዎችን ሊጠቀም ይችላል፡፡

5. ህጋዊ ሰውነት ወይም እውቅና ያላቸው በጥበቃ ቦታዎች ዙሪያ የሚገኙ የህብረተሰብ አቀፍ አደረጃጀቶች ከባለስልጣኑ ጋር በሚገቡት የውል ስምምነት መሠረት የሚከናወን የጋራ አስተዳደር ላይ የሰው ሃይል ቅጥር፣ ልማትና አመራር እንዲሁም የግዥ፣ ንብረትና ፋይናንስ አስተዳደር ሥራዎች ሥራዎች የሚፈጸሙት ለአስተባባሪ ኮሚቴ ቀርቦ በሚጸድቀው ዕቅድ መሰረት ሆኖ የሚከተሉትን ሰነዶች መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

ሀ) የተዋዋዮች ውል ስምምነት፡፡ እና

ለ) የሰው ሃይል፣ ፋይናንስና ንብረት ምደባና አስተዳርን በሚመለከት መንግስት ያወጣቸው ህጎች፡፡

## 13. በባለሥልጣኑ የሚደረጉ ድጋፎች፤

1. ባለሥልጣኑ አስፈላጊው ህጋዊ ሂደቶችን በማስፈጸምና መሰረታዊ የመሰረተ-ልማት አውታሮችን በመዘርጋት በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ምቹ የሥራ ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋል፤
2. የኢንቨስትመንት እና የግብር ሕጎችን መሰረት በማድረግ ከሚመለከታቸው መንግስታዊ ተቋማት ጋር በመተባበር የማበረታቻ አቅርቦቶችን ያመቻቻል፤
3. የአደጋ መከላከል እና ዝግጁነትን የሚያረጋግጡ የተለያዩ አሰራሮች በመዘርጋት እንዲተገበሩ ያደርጋል፤
4. ለፈንድ ማፈላለጊያ ስራዎች ውጤታማነት ድጋፎችን ያደርጋል፤
5. አጋርነትን የሚያጎለብት የድጋፍና ክትትል ስርዓት ይዘረጋል፤
6. ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም የሚያስችሉ ማንዋሎችና ማስተግበሪያ ቅጾችን ያዘጋጃል፡፡

## ምእራፍ ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 14. ስለተከለከሉ ተግባራት፤

1. የጥበቃ ቦታዎችን በባለቤትነት ማዛወር ወይም መሸጥ አይቻልም፤

2. ለትርፍ ያልተቋቋመ አጋር አካል ከባለስልጣኑ ጋር የሚገባው የጥበቃ ቦታዎች የጋራ አስተዳደር ውል ስምምነት ለሌላ ሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ የተከለከለ ነው፤

3. ለትርፍ የተቋቋመ አጋር አካል በሚገባው የውል ስምምነት ላይ ካልተመላከተ በስተቀር ከባለስልጣኑ ጋር በአጋርነት የጥበቃ ቦታውን ለማስተዳደር የገባውን የውል ቃል ወይም ስምምነት ለሌላ ሶስተኛ ወገን ለማስተላለፍ አይችልም፤

## 17. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ጸድቆ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት በውል ስምምነት መሠረት በስራ ላይ ያሉ ልዩ ልዩ የመንግስትና የግል አጋርነት ጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር ዓይነቶች በጋራ የውል ስምምነት ሰነዳቸው መሠረት መተዳደራቸው ጸንቶ ይቆያል፤

## 18. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ የመንግስትና የግል አጋርነት አስተዳደር መመሪያ ኮሚሽኑ በማናቸውም ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## 19. የተሻሩና ተፈጻሚ የማይሆኑ ህጎች

በዚህ መመሪያ በተመለከቱት የመንግስትና የግል አጋርነት ጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር ዝርዝር ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም መመሪያዎች ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

## 20. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ጸድቆ ከወጣበት-----ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ፕሮፌሰር ፍቃዱ በየነ

የአካባቢ፣ ደንና አየርንብረት ለውጥ ኮሚሽን

ኮሚሽነር